# ነአ በልዑል

ነአ ነአ ነአ ነአ በልዑል
የጌታ ባለሟል ቅዱስ ሚካኤል

ሰይጣን ሥልጣን ሲሻ አምላክ ለመሆን
ተለየ ከክብሩ ወርዶ ከዙፋን
በታማኝነትህ ፀንተህ በመቆምህ
በመላዕክት ላይ ልዑል አደረገህ

አዝ...

እስራኤላውያን በሙሴ ሲመሩ
ስላደረካቸው ክፉን እንዳይፈሩ
ባንተ ረዳትነት ተከፍሎ ባህሩ
ሁላቸው ባንድነት ሄዱ ተሻገሩ

አዝ...

ባህራን የዋህ ሰው የሞት ጥሪ ይዞ
ወደ አጥፊዎቹ አገር እያለ በጉዞ
በሰው ተመስለህ ፈጥነህ ደርሰህለት
የሞቱን ደብዳቤ በህይወት ለወጥክለት

አዝ...

የአፎምያን አባት አፅናኝ አለኝታዋ
ረዳቷ ነበረ መስለህ ጠባቂዋ
ባንተ ተመስሎ ሰይጣን ሲፈትናት
በሚያስፈራ ግርማህ ፈጥነህ ደረስክላት

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org